www.abyssinialaw.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 22
ADDIS ABABA 4th February 2009

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፷፩/፪ሺ፩
የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................................ ገፅ ፬ሺ፬፻፶፱

## CONTENTS

Regulation No. 161/2009
Coffee Quality Control And Transaction Council of Ministers Regulation.................................Page 4459

## ደንብ ቁጥር ፩፻፷፩/፪ሺ፩
## ስለ ቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በቡና ጥራት፣ ቁጥጥርና ግብይት አዋጅ ቁጥር ፮፻፪/፪ሺ አንቀጽ ፲፱(፩) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ «የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፩/፪ሺ፩» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

፩) «አዋጅ» ማለት የቡና ጥራት፣ ቁጥጥርና ግብይት አዋጅ ቁጥር ፮፻፪/፪ሺ ነው ፤

፪) «አግባብነት ያለው የክልል አካል» ማለት በቡና አምራች ክልል የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ወይም ተመሳሳይ ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው የክልል አካል ነው፤

፫) «የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከል» ማለት ጀንፈልና እሸት ቡና መገበያያ እንዲሆን አግባብነት ባለው የክልል አካል የተከለለ ሥፍራ ነው፤

፬) «አገልግሎት ሰጪ» ማለት በማንኛውም የቡና ግብይት ያልተሰማራ ሆኖ በቡና ማጠብ፣ መፈልፈል፣ ማበጠር፣ ማዘጋጀት፣ ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ አገልግሎት የተሠማራ ሰው ነው።

## Regulation No. 161/2009
## COFFEE QUALITY CONTROL AND TRANSACTION COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 19(1) of the Coffee Quality Control and Transaction Proclamation No. 602/2008.

### PART ONE
### GENERAL

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the " Coffee Quality Control and Transaction Council of Ministers Regulation No. 161/2009."

2. *Definition*

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1) "Proclamation" means the Coffee Quality Control and Transaction Proclamation No. 602/2008;

2) "appropriate regional organ" means agriculture and rural development bureau of a coffee producing region or any other organ of the region in charge of similar functions;

3) "primary coffee transaction center" means a place designated by the appropriate regional organ for trading red cherry and sun dried coffee;

4) "service provider" means any person not engaged in coffee transaction and engaged in washing, pulping, sifting, processing warehousing or transporting coffee.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፭) በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተመለከተው ትርጓሜ ለዚህ ደንብ አፈፃፀምም ተፈፃሚነት ይኖረዋል ፡፡

፫. የቀይ እሸትና የጀንፈል ቡና ግብይት

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት የሚደረግ የቀይ እሸትና የጀንፈል ቡና ግብይት፣ የራሳቸው ማሳ ባላቸው አነስተኛ አምራቾች ወይም ከአባላቱ የሰበሰቡትን ቡና በሚያቀርቡ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት እና በግብይት ማዕከላቱ የብቃት ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀት በተሰጣቸው አቅራቢዎች መካከል ብቻ ይከናወናል ፡፡

ለ) ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡናን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት የገዛ አቅራቢ ለሌላ አምራች ወይም አቅራቢ መልሶ መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡

፬. የአቅርቦትና ተረፈ ምርት ቡና ግብይት

፩/ የአቅርቦት ቡናና ተረፈ ምርት ቡና ግብይት በኢትዮጵያ የምርት ገበያ መድረክ ላይ ብቻ በገበያው አሠራር መሠረት ይከናወናል ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከፍተኛ ጥራት ላላቸውና የተሻለ ገቢ ለሚያስገኙ የአቅርቦት ቡናዎች ልዩ ማስተናገጃ ሥርዓት ሊያመቻች ይችላል ፡፡

፫/ የኢትዮጵያ ምርት ገበያው አባል የሆነ፦

ሀ) አቅራቢ በምርት ገበያው መድረክ የአቅርቦት ቡናን ከመሸጥ በስተቀር ማንኛውንም ቡና መግዛት ወይም መሸጥ አይፈቀድለትም፤

ለ) ቡና ላኪ በምርት ገበያው መድረክ ላይ ለውጪ ገበያ ዝግጅት የሚፈለገውን ደረጃን ያሟላ የአቅርቦት ቡናን ከመግዛትና ተረፈ ምርት ቡናን ከመሸጥ በስተቀር ማንኛውንም ቡና መግዛት ወይም መሸጥ አይፈቀድለትም፤

ሐ) የቡና ጅምላ ነጋዴ በምርት ገበያው መድረክ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል ቡናን ከመግዛት በስተቀር ማንኛውንም ቡና መግዛትም ሆነ መሸጥ አይፈቀድለትም፤

መ) ቡና ቆይ በገበያው መድረክ ላይ ለሥራው የሚያስፈልገውን የአቅርቦት ቡና ወይም ተረፈ ምርት ቡና ከመግዛት በስተቀር ማንኛውንም ቡና መሸጥ አይፈቀድለትም፡፡

፬. ወደ ቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል ቀርቦ ደረጃ የተሰጠው ቡና ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ እንደ ተገዛ በኋላ በድጋሚ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለሽያጭ መቅረብ የለበትም ፡፡

፭. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አባል የሆነ ሰው በገበያው መድረክ ላይ ቡና ለመግዛትም ሆነ ለመሸጥ የሚችለው በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የፀና የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀትና ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የፀና የቡና ንግድ ፈቃድ ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

5) The definition provided for under Article 2 of the Proclamation shall also be applicable for this Regulation.

3. *Transactions in Red Cherry and Sun Dried Coffee*

1) Red cherry and sun dried coffee trade in primary transaction centers shall be made between small products who harvest coffee from own farms or cooperatives that supply the coffee collected from their members and coffee suppliers certified by the trading center.

2) A supplier who buys red cherry or sun dried coffee pursuant to sub-article (1) of this Article shall not resell it to another producer or supplier.

4. *Transactions in Supply Coffee and Coffee By-products*

1) Transactions in supply coffee and coffee by-products shall take place only at the Ethiopia Commodity Exchange in accordance with the rules of the Exchange.

2) Without prejudice to sub-article (1) of this Article the Ethiopia Commodity Exchange may establish special arrangement for transaction of better quality and higher price supply coffee.

3) A member of the Ethiopia Commodity Exchange who is:

(a) a coffee supplier my not be allowed to buy or sell coffee at the Exchange other than selling supply coffee;

(b) a coffee exporter my not be allowed to buy or sell coffee at the Exchange other than buying supply coffee that has export quality and selling coffee by-products;

(c) a coffee wholesaler my not be allowed to buy or sell coffee at the Exchange other than buying domestic consumption coffee;

(d) Coffee roaster my not be allowed to buy or sell coffee at the Exchange other than buying supply coffee or coffee by-product that is required for its operations.

4) Coffee graded by the coffee liquoring center and sold at the Exchange may not be introduced for re-sale at the Exchange.

5) Any member of the Exchange shall be allowed to buy or sale coffee at the Exchange only upon presentation of a valid certificate of competence issued in accordance with this Regulation and a valid coffee trade license issued by the competent organ.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል ሁለት

## ስለመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት

፭. ስለመከለል

፩. አግባብነት ያለው የክልል አካል በግብይት ጉዳይ በሕግ ሥልጣን ከተሰጣቸው ሌሎች የክልሉ አካላት ጋር በመመካከር በቡና አምራች አካባቢ የሚከለሉትን የመጀመሪያ ደረጃ የቡና የግብይት ማዕከላትን ብዛትና ሥርጭት ይወስናል፡፡

፪. አግባብነት ያለው የክልል አካል በየቡና አምራች አካባቢው ሊኖር የሚገባውን የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት ብዛትና ስርጭት ሲወስን የሚከተሉትን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ) ለቡና አምራቾችና አቅራቢዎች ያላቸውን ቀረቤታ፤

ለ) ተሽከርካሪን ለማስገባትና ለማስወጣት ያላቸው አመቺነት፤

ሐ) ከግብይት በኋላ ቡናውን ከ፲፪ ሰዓት ባል በለጠ ጊዜ ለቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ለማቅረብ ያላቸውን አመቺነት፤

መ) በባሕሪያቸው ተመሳሳይ ለሆኑ የቀይ እሸትና የጀንፈል ቡና ምርቶችን ለመገበያየት ያላቸውን አመቺነት ፤

ሠ) ለቀይ እሸት ቡና ግብይት አገልግሎት ለመ ሥጠት ያላቸው አመቺነት፣ እና

ረ) ከትምህርት ቤቶች፣ ከጤናና ከእምነት ተቋማት ቦታዎች በበቂ ርቀት ላይ መገኘታቸውን፡፡

፫. የግብይት ማዕከል ለአጐራባች ወረዳዎች የሚያገ ለግል ሲሆን አከላለሉ አግባብነት ባለው የክልል አካልና በአጐራባች ወረዳዎቹ የግብርናና ገጠር ልማት ጽሕፈት ቤቶች በጋራ ይወሰናል፡፡

፮. የግብይት ቀንና ሰዓት

፩. የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከል የገበያ ቀንና ሰዓት የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ ገብቶ በዚህ ደንብ መሠረት የግብይት ማዕከሉን በከለለው አካል ይወሰናል፡፡

፪. የሚቻል በሆነ ጊዜ ሁሉ የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከል የገበያ ቀንና ሰዓት ከሌሎች የገበያ ቦታዎች ቀንና ሰዓት የተለየ መሆን ይኖርበታል፡፡

፯. ስለመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት አደረጃጀት

፩. የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከል፡-

ሀ) ቢያንስ ፶ በ፶ ሜትር ስፋት ያለው፤

ለ) በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁስን በመጠቀም የተገነባ አጥር ያለው፤

ሐ) የገበያ መረጃ ሠሌዳን፣ መጫኛና ማራገፊያ መደላድልን፣ ደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያና፣ የደረቅ መፀዳጃ ቤትን ያጠቃለለ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ያለው፤

መ) በእያንዳንዱ አቅራቢ ወይም አምራች በባለ ቤትነት የተያዘ በኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የተመሠከረለት ሚዛን ያለው፣ እና

*PART TWO*

*PRIMARY COFFEE TRANSACTION CENTERS*

5. *Designation*

1) The appropriate regional organ shall, in consultation with other organs of the region vested with the power of regulating trade, determine the number and distribution of primary transaction centers to be designated in coffee producing localities.

2) When determining the number and distribution of primary transaction centers the following consideration shall be taken into account:

(a) proximity for coffee producers and suppliers;

(b) convenience for entrance and exit of motor vehicle;

(c) convenience for transporting the coffee to processing plants within 12 hours after transaction;

(d) convenience for trading red cherry and sun dried coffee sharing similar properties;

(e) convenience for giving services for transaction of red cherry coffee; and

(f) sufficiency of distance from schools, health and religious institutions.

3) Where a transaction center serves neighboring woredas, the designation shall be determined jointly by the appropriate regional organ and the agriculture and rural development offices of the concerned woredas.

6. *Transaction Days and Hours*

1) The trading days and hours of a primary transaction center shall be determined by the organ which designated it pursuant to this Regulation with due regard to the objective conditions of the locality.

2) The trading days and hours of a primary transaction center shall, to the extent possible, be separate from days and hours of other trading places.

7. *Organization of Primary Transaction Center*

1) A transaction center shall:

(a) have a dimension of at least 50 by 50 meters;

(b) be fenced by using locally available materials;

(c) have a common service comprising market data board, loading and unloading platform, dry waste burring and pit latrine;

(d) have weighing scale certified by the Quality and Standards Authority of Ethiopia and owned by each of the suppliers; and

ሠ) ዕዳ፡ የተጠበቀና ለመረጃ አገልግሎት የተመቻቸ፣ መሆን ይኖርበታል ።

፪. የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል የገበያ ቦታን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል ቦታው በቡና ጥራት ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ የአካባቢው ሁኔታዎች ነፃ እንዲሆን ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት።

## ክፍል ሦስት

## ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

፰. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

ማንኛውም ቡና አቅራቢ፣ ላኪ ፣ ጅምላ ነጋዴ፣ ቡና ቆይ፣ አዘጋጅ ወይም የቡና መጋዘን አገልግሎት ሰጪ ለንግድ ፈቃድ ከማመልከቱ በፊት በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት ።

፱. የቡና አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

የቡና አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ፦

፩. ሚኒስቴሩ ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው የቡና ማከማቻ መጋዘን ፣ የቡና መፈልፈያ፣ ማጠቢያና ማድረቂያ መሣሪያ፣ ከረጢት እና ሌሎች አስፈላጊ መሣሪያዎች ያሉት መሆኑ፣

፪. በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይም በውል መሠረት ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛንና የእርጥበት መቆጣጠሪያ መሣሪያ ያሉት መሆኑ፣

፫. የታጠበ ቡና አቅራቢ ሲሆን ሚኒስቴሩ ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም በውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ቋሚ ፍሰት ባለው ወንዝ ወይም በቂ ውሃ በሚገኝበት ቦታ የሚገኝ የቡና ማዘጋጃ ድርጅት ያለው መሆኑ፣

፬. ቡናን በማዘጋጀት ሂደት በተፈጥሮ አካባቢ፣ በአካባቢው በሚገኝ ማኅበረሰብ ወይም በግለሰብ ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳኋን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሠራር ያለው መሆኑ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠለት መሆኑ፣

፭. ባሕሪያቸው የተለያዩ የቡና ዓይነቶችን እንደ ባህሪያቸው ለማዘጋጀት የሚያስችል አሰራር የዘረጋ መሆኑ፣

፮. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ፣ እና

፯. ከቡና ጥራት ጋር በተያያዘ በቂ ዕውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሰማራ መሆኑ፣

ሲረጋገጥ ይሆናል ።

(e) be clean and convenient for information technology services.

2) The organ in charge of administering the trading places of a primary transaction center shall take the necessary measures to clean them from environmental effects that may affect the quality of coffee.

## PART THREE

## CERTIFICATE OF COMPETENCE

8. *Requirement of Certificate of Competence*

Any coffee supplier, exporter, wholesaler, roaster, processor or coffee warehouse operator shall obtain a certificate of competence issued in accordance with this Regulation prior to applying for a trade license.

9. *Coffee Supplier's Certificate of Competence*

A coffee supplier's certificate of competence shall be granted upon ascertaining that the applicant:

1) owns or has procured from a third party through a lease contract a warehouse, a coffee pulping, washing and drying machines, bags and other necessary materials which meet the technical standards set by the Ministry;

2) owns or has procured from a third party through a lease contract a weighing scale and moisture calibrator verified by the Quality and Standards Authority of Ethiopia;

3) in case of a washed coffee supplier, owns or has leased from a third party a coffee processing plant that meets operational standards set by the Ministry or the appropriate regional organ and is located along a permanent drainage basin or a sufficient supply of water;

4) arranges operational processes, as confirmed by the competent authority, that can dispose wastes without causing harm to the environment, the public or individuals;

5) has an operational procedures to process coffee products of different ecological properties separately;

6) owns a service catering office organized in a manner to be able to provide the necessary services; and

7) has permanently deployed a staff sufficiently qualified in coffee quality matters.

www.abyssinialaw.com



## ፲. የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

የቡና ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ፦

፩. የአቅርቦት ቡናን ለውጪ ገበያ አዘጋጅቶ ለመላክ የሚገለገልበት በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚኒስቴሩ ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ የቡና ማከማቻ መጋዘን፣ የቡና መፈልፈያ፣ ማጠቢያ፣ ማድረቂያ፣ ማበጠሪያና ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎች ያሉት መሆኑ፣

፪. በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛንና የእርጥበት መቆጣጠሪያ መሣሪያ ያሉት መሆኑ፣

፫. ቡናን በማዘጋጀት ሂደት በተፈጥሮ አካባቢ፣ በአካባቢው በሚገኝ ማህበረሰብ ወይም በግለሰብ ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳኋን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሠራር ያለው መሆኑ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠለት መሆኑ፣

፬. ወደውጭ ሀገር ለመላክ የገዛውን፣ ለጅምላ ሻጭ ነጋዴ የሸጠውንና በመጋዘን የቀረውን የቡና ክምችት በዓይነትና በመጠን ለይቶ ቢያንስ በየወሩ መጨረሻ ላይ ለሚኒስቴሩ የሚያሳውቅበት የመረጃ ፍሰት ሥርዓት የዘረጋ መሆኑ፣

፭. የተለያየ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸው የቡና ዓይነቶች ቀይጦ የሚልክ በሆነ ጊዜ ለዚሁ ሥራ ከሚኒስቴሩ የተሰጠውን ልዩ ፈቃድ ያቀረበ መሆኑ፣

፮. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ ፤ እና

፯. ከቡና ጥራት ጋር በተያያዘ በቂ ዕውቀት ያለው ባለሙያ ያሰማራ መሆኑ፣

ሲረጋገጥ ይሆናል ፡፡

## ፲፩. የቡና አዘጋጅነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

የቡና አዘጋጅነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ፦

፩. ሚኒስቴሩ ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም ከሶስተኛ ወገን በኪራይ ያገኘው የማከማቻ መጋዘንና የቡና መፈልፈያ፣ ማጠቢያ፣ ማድረቂያ፣ ማበጠሪያና ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ መሣሪያዎች ያሉት መሆኑ ፣

፪. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ፣

፫. ከቡና ጥራት ጋር በተያያዘ በቂ ዕውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሰማራ መሆኑ ፣

## 10. *Coffee Exporter's Certificate of Competence*

A coffee exporter's certificate of competence shall be granted upon ascertaining that the applicant:

1) owns or has leased from a third party a coffee warehouse and sifting and other necessary equipment that meet the technical standards set by the Ministry;

2) owns or has leased from a third party a weighing scale and a moisture calibration instrument certified by the Quality and Standards Authority of Ethiopia;

3) arranges operational processes, as confirmed by the competent authority, that can dispose wastes without causing harm to the environment, the public or individuals;

4) has an information flow mechanism through which he can inform the Ministry, at least at the end of every month, about the type and quantity of coffee purchased for export, sold to wholesales and the stock balance remaining in the warehouse;

5) has produced a special license granted by the Ministry if he exports blended coffees that have different properties or standards;

6) owns a service catering office organized in a manner to be able to provide the necessary services; and

7) has permanently deployed a staff sufficiently qualified in coffee quality matters.

## 11. *Coffee Processor's Certificate of Competence*

A coffee processor's certificate of competence shall be granted upon ascertaining that the applicant:

1) owns or has leased from a third party a warehouse, a coffee pulping, washing, drying, sifting and other machines that meet the technical standards set by the Ministry;

2) owns a service catering office organized in a manner to be able to provide the necessary services;

3) has permanently deployed a staff sufficiently qualified in coffee quality matters;

፬. የታጠበ ቡና አዘጋጅ ከሆነ ሚኒስቴሩ ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም በውል መሠረት ከሶስተኛ ወገን ያገኘው ቋሚ ፍሰት ባለው ወንዝ ወይም በቂ ውሃ በሚገኝበት ቦታ የሚገኝ የቡና ማዘጋጃ ድርጅት ያለው መሆኑ፣

፭. በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛንና የእርጥበት መቆጣጠሪያ መሣሪያ ያሉት መሆኑ፣

፮. ቡናን በማዘጋጀት ሂደት በተፈጥሮ አካባቢ፣ በአካባቢው በሚገኝ ማህበረሰብ ወይም በግለሰብ ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳኋን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሰራር ያለው መሆኑ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠለት መሆኑ፣ እና

፯. የተለያየ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን ቡናዎች ለመለየት የሚያስችለው አሠራር ያለው መሆኑ፣

ሲረጋገጥ ይሆናል ፡፡

**፲፪. የቡና ማከማቻ መጋዘን አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**

የቡና ማከማቻ መጋዘን አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ፦

፩. ሚኒስቴሩ ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሶስተኛ ወገን ያገኘው የቡና ማከማቻ መጋዘን ያለው መሆኑ፣

፪. የተለያዩ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን ቡናዎች ለመለየት የሚያስችለው አሰራር ያለው መሆኑ፣ እና

፫. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎ መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ፣

ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

**፲፫. የቡና ጅምላ ነጋዴነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**

የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡናን በመግዛት ለቸርቻሪ ነጋዴዎች ለመሸጥ የሚያስችል የቡና ጅምላ ነጋዴነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ፦

፩. ሚኒስቴሩ ያወጣቸውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሶስተኛ ወገን ያገኘው የቡና ማከማቻ መጋዘንና ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎች ያሉት መሆኑ፣

፪. በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን ያለው መሆኑ፣ እና

፫. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ፣

ሲረጋገጥ ይሆናል ፡፡

4) in case of a washed coffee processor, owns or has leased from a third party a coffee processing plant that meets operational standards set by the Ministry and is located along a permanent drainage basin or a sufficient supply of water;

5) owns or has leased from a third party a washing scale and a moisture calibration instrument certified by the Quality and Standards Authority of Ethiopia.

6) arranges operational processes, as confirmed by the competent authority, that can dispose wastes without causing harm to the environment, the public or individuals; and

7) employs procedures that enable to differentiate coffee beans that have various characteristics or standards.

*12. Coffee Warehouse Operator's Certificate of Competence*

A coffee warehouse operator's certificate of competence shall be granted upon ascertaining that the applicant:

1) owns or has leased a coffee warehouse that meets the technical standards set by the Ministry;

2) employs procedures that enable to differentiate coffee beans that have different properties or standards; and

3) owns a service catering office organized in a manner to be able to provide the necessary services.

*13. Coffee Wholesaler's Certificate of Competence*

A coffee wholesaler's certificate of competence, which enables to supply domestic consumption coffee to retailers, shall be granted upon ascertaining that the applicant:

1) owns or has leased from a third party a coffee warehouse and other necessary equipment that meet technical standards set by the Ministry;

2) owns or has leased from a third party a weighing scale certified by the Quality and Standards Authority of Ethiopia: and

3) owns a service catering office organized in a manner to be able to provide the necessary services.

www.abyssinialaw.com



፲፬. የቡና ቆይ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

የቡና ቆይ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ፦

ሀ. ሚኒስቴሩ ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል ከሦስተኛ ወገን ያገኘው የቡና ማከማቻ መጋዘን፣ የቡና መቁያ፣ መፍጫ፣ ማሸጊያና ሌሎች ለሥራው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ያሉት መሆኑ፣

ለ. ከቡና ጥራት ጋር በተያያዘ በቂ ዕውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሠማራ መሆኑ፣ እና

ሐ. በምርቱ ማሸጊያ ላይ የምርቶቹን ዓይነት፣ ባህሪና ጥራት ደረጃ የሚያንፀባርቁ ፅሁፎችን ለማስቀመጥ የሚያስችል አሠራር ያለው መሆኑ፣

ሲረጋገጥ ይሆናል።

፲፭. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩. በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ማመልከቻውን አግባብነት ላለው የክልል አካል ወይም ቡና ላኪንትን የሚመለከት ሲሆን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት።

፪. ማመልከቻው የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በዚህ ደንብ የተደነገጉት መስፈርቶች መሟላታቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎችንና ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን መያዝ አለበት።

፫. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል ማመልከቻው በደረሰው በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ በቀረበለት ጥያቄ ላይ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል።

፬. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል አመልካቹ የብቃት ማረጋገጫው የማይገባው መሆኑን በወሰነ ጊዜ የከለከለበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ በዝርዝር ማስቀመጥ ይኖርበታል።

፭. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል በሰጠው ውሳኔ በሕግ ጉዳይ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔው በተሰጠው በ፳ የሥራ ቀናት ውስጥ እንዳግባቡ ለፌዴራል ወይም ለክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል።

፲፮. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድና መሠረዝ

፩. በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፦

ሀ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠባቸውን መስፈርቶች አንድሎ ሲገኝ፣ ወይም

14. *Coffee Roaster's Certificate of Competence*

A coffee roaster's certificate of competence shall be granted upon ascertaining that the applicant:

1) owns or has leased from a third party a coffee warehouse, coffee roasting, grinding, packing and other equipment that meet the technical standards set by the Ministry;

2) has permanently deployed a staff sufficiently qualified in coffee quality matters; and

3) has arrangements for labeling the product to indicate its type, properties and quality standards on the package.

15. *Application for Certificate of Competence*

1) Any person who wants to obtain a certificate of competence to be issued in accordance with this Regulation shall submit his application to the appropriate regional organ or, in case of coffee exporter, to the Ministry.

2) The application shall contain evidences showing the fulfillment of the requirements provided for in this Regulation with respect to the issuance of the certificate of competence in question and other information that may be required pursuant to directives issued by the Ministry or the appropriate regional organ.

3) The Ministry or the appropriate regional organ shall decide on the application within 15 working days from the date of receipt of the application.

4) When the Ministry or the appropriate regional organ rejects the application, it shall state, in detail, the reasons for the rejection.

5) Any applicant who is dissatisfied with the decision of the Ministry or the appropriate regional organ may appeal, on question of law, to the federal or regional high court, as appropriate, within 20 working days from the date of receipt of the decision. The decision of the court shall be final.

16. *Suspension and Revocation of Certificate of Competence*

1) Where a person issued with a certificate of competence in accordance with this Regulation:

(a) fails to maintain the conditions upon the basis of which the certificate of competence has been issued; or

8 www.abyssinialaw.com



ለ) የአዋጁን ወይም የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁንና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን ተላልፎ ሲገኝ፤

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል ጉድለቶቹን ተገቢ በሆነና ተለይቶ በተገለጸ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያስተካክል በማስገንዘብ የምስክር ወረቀቱን አግዶ ሊያቆየው ይችላል፡፡

፪ በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው፡-

ሀ) የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሃሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ሆኖ ከተገኘ፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለምስክር ወረቀቱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፤ ወይም

ሐ) የአዋጁን አንቀጽ ፲፭ በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽሞ ከተገኘ፤

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው የክልል አካል ሊሠረዝ ይችላል፡፡

፫. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሠረዘበት ሰው በሕግ ጉዳይ ላይ ቅሬታ ካለው ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት ፷ ቀናት ውስጥ እንደሚገባው ለፌደራሉ ወይም ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

፲፯. የእግድ ወይም የመሠረዝ ውጤት

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ መሠት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በዕገዳው ወይም በመሰረዙ ላይ የቀረበው ይግባኝ በመታየት ላይ እያለ ቢሆንም በቡና ግብይት ላይ ሊሠማራ አይችልም፡፡

፪ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በዚህ ደንብ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ መገልገያዎቹን ፣ መሣሪያዎቹንና እቃዎቹን የሀና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ሌላ ሰው እንዲጠቀምባቸው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

ክፍል አራት

የቡና ጥራትና ግብይት ቁጥጥር

፲፰ ክልከላ

ለማንኛውም ቡና አምራች ወይም አዘጋጅ በቡና ለቀማ፣ ዝግጅትና፣ አቀራረብ ሂደት ላይ፡-

፩ ቡናን በአፈር ማሸት ወይም ከባዕድ ነገር ጋር ማደባለቅ፣

፪ ክብደቱ እንዲጨምር ቡናን በውሃ መዘፍዘፍ፣

(b) contravenes the provisions of the Proclamation or this Regulation or directives issued for the implementation of the Proclamation and this Regulation,

the Ministry or the appropriate regional organ may suspend the certificate of competence and instruct such person to rectify the irregularities within a specified reasonable period of time.

2) Where the holder of a certificate of competence issued in accordance with this Regulation:

(a) is found to have obtained the certificate of competence upon presentation of false evidence,

(b) fails to rectify the irregularities which caused the suspension of the certificate of competence pursuant to sub-article (1) of this Article within the specified time limit, or

(c) has committed a criminal offence in violation of Article 15 of the Proclamation,

the Ministry or the appropriate regional organ may revoke the certificate of competence.

3) A person who is aggrieved at the suspension or revocation of his certificate of competence may appeal, on question of law, to the federal or regional high court, as appropriate, within 60 days from the date of receipt of the decision. The decision of the court shall be final.

17. *Consequences of Suspension or Revocation*

1) A person whose certificate of competence has been suspended or revoked pursuant to Article 16 of this Regulation shall not engage in coffee transaction irrespective of the fact that his appeal against the suspension or revocation is under consideration.

2) Notwithstanding sub-article (1) of this Article, a person whose certificate of competence has been suspended or revoked may authorize the use of his facilities, machineries and equipment that fulfill the requirements of this Regulation by another person holding a valid certificate of competence.

*PART FOUR*

*INSPECTION OF COFFEE QUALITY AND TRANSACTION*

18. *Prohibitions*

It is prohibited for any coffee producer or processor, in the course of collecting processing or supplying coffee, to:

1) jumble coffee with soil or mix coffee with alien substances;

2) place coffee into water with intent to increase its weight;

www.abyssinialaw.com

፫. ቡናን በመኪና መንገድ ላይ በመዘርዘር ማስጨፍለቅ ፣

፬. ያልደረሰ እሸት ቡናን መሸምጠጥ ወይም ቀይ እሸት ቡናን ከአረንጓዴ ወይም ቢጫ ቡና ጋር መቀላቀል፣

፭. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል አገልግሎት ላይ እንዲውል ከወሰነው የቡና ከረጢት ወይም ሌላ መሣሪያ ውጪ መጠቀም፣ ወይም

፮ በቡና ማሳው ላይ በባለሙያ ያልተመሰከረለት ኬሚካል መጠቀም፣ የተከለከለ ነው፡፡

፲፱. የቡና ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪዎችን ስለመመደብ

፩. እንደ አግባቡ ሚኒስቴሩና አግባብነት ያላቸው የክልል አካላት የቡና ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪዎችን ይመድባሉ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚመደብ የቡና ተቆጣጣሪ ስለቡና ጥራትና ግብይት በቂ ዕውቀት ያለውና በመልካም ሥነ-ምግባሩ የተመሠከረለት መሆን ይኖርበታል፡፡

፳. የቡና ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ መሠረት የተመደበ የቡና ጥርትና ግብይት ተቆጣጣሪ፣ የአዋጁና የዚህ ደንብ ድንጋጌዎችና አዋጁንና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ:-

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት የሚካሄደውን የቡና ንግድ፣

ለ) በቡና አምራች ባለሀብቶች የሚካሄደውን የቡና አመራረትና አዘገጃጀት፣

ሐ) በቡና አቅራቢዎች፣ ላኪዎችና አዘጋጆች የሚከናወነውን የቡና ዝግጅት፣

መ) በቡና አቅራቢዎች፣ ላኪዎችና አጓጓዦች የሚደረገውን የቡና ማጓጓዝ፣

ሠ) የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና አሻሻጥን፣

የመቆጣጠር ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፪. የቡና ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ኃላፊነቱን ለመወጣት:-

ሀ) ወደ ማንኛውም የቡና መጋዘን፣ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም የአገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቦታ በሥራ ሰዓት ለመግባትና አግባብነት ያላቸውን ሠነዶች ለመመልከትና ኮፒ ለመውሰድ፣ ፎቶግራፍ ለማንሳት የቡና ናሙና ለመውሰድ፣

ለ) ቡና የሚያጓጓዝ ተሽከርካሪን በማስቆም ለመፈተሽና አግባብነት ያላቸው ሠነዶች እንዲቀርቡለት ለመጠየቅ፣ እና

3) scatter coffee on road for pulping;

4) pick immature coffee or mix red cherry with green or yellow coffee;

5) use coffee sacks or equipment other than those approved by the Ministry or the appropriate regional organ; or

6) use chemicals not verified by professionals on the coffee farm.

*19. Assignment of Coffee Quality and Transaction Inspectors*

1) The Ministry and the appropriate regional organs shall, as may be appropriate, assign coffee quality and transaction inspectors.

2) A person to be assigned as inspector pursuant to sub-article (1) of this Article shall have adequate knowledge on coffee quality and transactions and proves ethical background.

*20. Powers and Duties of Coffee Quality and Transaction Inspectors*

1) A coffee quality and transaction inspector assigned pursuant to Article 19 of this Regulation shall have the powers and duties to inspect:

(a) coffee transactions at primary coffee transaction centers;

(b) production and processing of coffee by investors;

(c) processing of coffee by suppliers, exporters and processors;

(d) transportation of coffee by suppliers, exporters and carriers, and

(e) sales of domestic consumption coffee;

for the purpose of ensuring compliance with the provisions of the Proclamation and this Regulation and directives issued for the implementation of the Proclamation and this Regulation.

2) A coffee quality and transaction inspector may, in the course of discharging his responsibilities under sub-article (1) of this Article:

(a) enter, during working hours, any coffee warehouse, processing plant or the site of a service provider and examine and take copies of relevant documents, take photographic evidences and samples of coffee; and

(b) stop and inspect any vehicle transporting coffee and demand the presentation of pertinent documents; and

www.abyssinialaw.com



(ሐ) ከአቅራቢ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚጓጓዝ ቡና ሲጫን በጥራት፣ በእርጥበቱና በዓይነቱ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ ማድረግ፣ ይችላል።

፫. የቡና ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪ የአዋጁ ወይም የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁንና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች መጣሳቸውን ሲያረጋግጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ትዕዛዙን ለማውጣት በሚያስፈልገው ጊዜ ውስጥ ቡናው ሊሠወር ይችላል ብሎ ሲገመት ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሕገ ወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ቡና ደረሰኝ ሰጥቶ የመያዝ ወይም የቡናውን ናሙና ወስዶ ቡናው የተከማቸበትን መጋዘን የማሸግ ሥልጣን ይኖረዋል።

፬. የቡና ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ስለወሰደው እርምጃ ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል ሪፖርት ማድረግና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፪ መሠረት መወሰድ ስላለባቸው ተከታታይ እርምጃዎች ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው የክልሉ አካል የሚሰጠውን መመሪያ መፈጸም አለበት።

፳፩. ሕገ ወጥ ድርጊቶችን ስለመጠቆም

፩. ማንኛውም ሰው በቡና አዘገጃጀት፣ ክምችት፣ ማጓጓዝ ወይም ግብይት ሂደት የአዋጁን ወይም የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁንና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ሕገ ወጥ ድርጊት መፈጸሙን ሲያውቅ በአካባቢው ለሚገኝ የቡና ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪ ወይም ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል በጽሑፍ መጠቆም ይችላል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ (፩) መሠረት ጥቆማ አቅርቦ ሕገ ወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ቡና ያስያዘ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፬) (ለ) መሠረት የጠቋሚ አበል ይከፈለዋል።

፳፪. ስለተያዘ ቡና

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ቡናው የተያዘበት ወይም የቡና መጋዘኑ የታሸገበት ማንኛውም ሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልሉ አካል ሊያቀርብ ይችላል።

፪. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልሉ አካል ተቃውሞውን ከአንድ ሣምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል። የሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል ውሳኔ፣

(c) make preliminary inspection on the quality, moisture and type of coffee, at the time of its loading, to be transported from suppliers to the Ethiopia Commodity Exchange.

3) Where a coffee quality and transaction inspector ascertains that the provisions of the Proclamation or this Regulation or directives issued for the implementation of the Proclamation and this Regulation are contravened, he shall have the power, with a court warrant or without court warrant if he believes that the coffee may be removed during the time required for obtaining the court warrant, to seize, against issuance of a receipt, the illegally handled coffee or take sample of the coffee and seal the warehouse where the coffee is deposited.

4) The coffee quality and transaction inspector shall immediately report to the Ministry or the appropriate regional organ on the action he has taken pursuant to sub-article (3) of this Article and follow the instructions of the Ministry or the appropriate regional organ for taking subsequent actions in according with Article 22 of this Regulation.

21. *Whistle Blowing Illegal Acts*

1) Any person who is aware of an illegal act committed, in violation of the provisions of the Proclamation or this Regulation or directives issued for the implementation of the Proclamation and this Regulation, in the course of processing, storing or transporting coffee or in the course of coffee transaction may report the same, in writing, to the nearest coffee quality and transaction inspector or to the Ministry or the appropriate regional organ.

2) Any person who has submitted a report in accordance with sub-article (1) of this Article that led to the seizure of coffee subject to the illegal act shall be entitled to the payment of whistle blower's commission pursuant to sub-article (4)(b) of Article 22 of this Regulation.

22. *Seized Coffee*

1) Any person whose coffee is seized or coffee warehouse is sealed pursuant to sub-article (3) of Article 20 of this Regulation may submit his objection to the Ministry or appropriate regional organ within five working days.

2) The Ministry or the appropriate regional organ shall, within one week, examine and decide on the objection. Where the decision of the Ministry or the appropriate regional organ:

www.abyssinialaw.com

ሀ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የማይሽር ከሆነ ወዲያውኑ የተያዘው ቡና ለአመልካቹ እንዲመለስ ወይም በቡናው የተከማቸበት መጋዘን እሽግ እንዲነሳ ይደረጋል፤ ወይም

ለ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚያጸና ከሆነ የቡናውን ናሙና በማስቀረት ቡናው ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ የቡና የግብይት ማዕከላት ቡናን ለመግዛት ለተፈቀደለት አቅራቢ፣ የተዘጋጀ የአቅርቦት ቡና ከሆነ ለቡና ላኪ፣ የሀገር ውስጥ ፍጆታ ቡና ከሆነ ጅምላ ሻጭ ወይም ለቆይና ፈጭቶ ሻጭ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል እንዲሸጥ ተደርጎ ገንዘቡ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው የክልል አካል በተከፈተ ገዥ የባንክ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ) የተመለከተውን ውሳኔ የሚቃወም የቡና ባለቤት ውሳኔው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ይግባኙን እንደአግባቡ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት፡-

ሀ) የሚኒስቴሩን ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል የሰጠውን ውሳኔ ከሻረው ቡናውን ለመሸጥ የወጣው ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሽያጩ ገንዘብ ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረጋል፤ ወይም

ለ) ውሳኔውን ካጸናው ወይም ባለቡናው በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ ካላቀረበ ለጠቋሚ የሚከፈል አበል ካለ ተቀንሶ የሽያጩ ገንዘብ እንደአግባቡ ለፌዴራሉ ወይም ለክልሉ መንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

(a) disapproves the actions of the inspector, the release of the seized coffee or the opening of the sealed coffee warehouse shall be immediately effected;

(b) approves the actions of the inspector, the coffee shall, after retaining sample, be sold to a supplier authorized to buy coffee at a primary coffee transaction center where it is red cherry or sun dried, to an exporter where it is supply coffee or to a wholesaler or coffee roaster where it is domestic consumption coffee at the Ethiopia Commodity Exchange, and the proceeds of the sale shall be deposited in a blocked bank account opened in the name of the Ministry or the appropriate regional organ.

3) The owner of coffee who objects the decision referred to in sub-article (2)(b) of this Article may lodge his appeal to the federal high court or the regional high court, as appropriate, within 30 days from the date of receipt of the decision.

4) Where the court to which an appeal is submitted pursuant to sub-article (3) of this Article:

(a) reverses the decision of the Ministry or the appropriate regional organ, the proceeds of the sale shall, after deducting the cost of sales, be paid to the owner of the coffee; or

(b) upholds the decision, or the owner fails to submit an appeal within the specified time limit, the proceeds of the sale shall, after deducting the amount of commission to be paid to whistle blowers, if any, be transferred to the federal or regional government, as appropriate.

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፫. የመተባበር ግዴታ

፩. ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው የክልል አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፪. የቡና ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሕገ ወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ቡና ለመያዝ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ፖሊስ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

## *PART FIVE*
## *MISCELLANEOUS PROVISIONS*

### 23. *Duty to Cooperate*

1) Any person shall have the duty to cooperate with the Ministry or the appropriate regional organ in the implementation of this Regulation.

2) Police shall provide the necessary assistance to a coffee quality and transaction inspector in seizing, pursuant to sub-article (3) of Article 20 of this Regulation, coffee subjected to illegal acts.

www.abyssinialaw.com



፳፬. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ማንኛውም ቡና አቅራቢ፣ ላኪ፣ ጅምላ ነጋዴ፣ ቡና ቆይ፣ አዘጋጅ ወይም የቡና መጋዘን አገልግሎት ሰጪ ይህ ደንብ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እስኪያገኝ ድረስ ባለው የጸና የንግድ ፍቃድ ሥራውን ማካሄድ ይችላል፡፡

፳፭. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፳፮. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከህዳር ፭ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

24. *Transitory Provision*

Any coffee supplier, exporter, wholesaler, roaster, processor or coffee warehouse operator shall continue operating his business using his existing valid trade license until he obtains a certificate of competence from the Ministry or the appropriate regional organ within six months from the effective date of this Regulation.

25. *Inapplicable Regulations and Directives*

No regulation or directive shall, in so far as they are inconsistent with this Regulation, be applicable with respect to matters provided for by this Regulation.

26. *Effective Date*

This Regulation shall enter into force as on the 14th day of November, 2008.

Done at Addis Ababa, this 4th day of February 2009.

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*